# የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል

ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበር
የቆመ ሕዝባዊ ሠራዊትና ሕዝባዊ ታጋይ የፖለቲካ፣ የስነ ሥርዓትና
የስነምግባር አጭር መመሪያ።

www.ginbot7pf.org

**መግቢያ**

ዛሬ በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣንና የኢኮኖሚ ሃብት ሙሉ በሙሉ የተያዘው በዘረኛነቱ፣ በዘራፊነቱ በታሪካችን ተወዳዳሪ በማይገኝለት በወያኔ እጅ ነው። ወያኔ ደግሞ በሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ህይወት ላይ ያሻኘን የማድረግ መብት አለኝ ብሎ የሚያምን ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሃገር የሆነ ስብስብ ነው። በእንዲህ አይነቱ የአፈናና የሃብት ጡንቻው ከፈረጠመ ጨካኝ አገዛዝ ጋር ታግሎ ሕዝብ ለዘመናት ሲናፍቀው የኖረውን የህግ የበላይነት የሰፈነበት፣ ዜጎች በነፃነት፣ በእኩልነት፣ በሰላምና በብልጽግና የሚኖሩበትን ሃገር ለመፍጠር መራራ ትግል እንደሚጠይቅ ባለፉት ዓመታት ከወያኔ ጋር ከተደረጉ የራሳችንና የወገኖቻችን የትግል ተመክሮ የተረዳነው ሃቅ ሆኗል።

ይህ አይነቱ መራራ ትግል በተለያዩ ቦታዎችና ወቅቶች በታሪክ እንደታየው በጥቂቶች ይጀመር እንጂ ጉዳዩ በዋንኛነት የሚመለከተውን ሕዝብ በሰፋት ሳያሳትፍና የሕዝብን አመኔታና ድጋፍ ሳያገኝ የትም ሊደርስ እንደማይችል የታወቀ ነው። በሥልጣን ላይ የሚገኙ አምባገነን ገዥዎች ለወታደሮቻቸውና ለሰላዮቻቸው ባስታጠቁት መሳሪያና ለቅጥረኞቻቸው በሚከፍሉት ከሕዝብ በተዘረፈ ሃብት ሁሌም አሸናፊ ሆነን በሥልጣን እንቀጥላለን ብለው እንደሚያምኑ ሁሉ፤ በእጁ ምንም ሃብትና መሳሪያ የሌለው ጭቆናን ተቃውሞ የሚነሳው ታጋይ ግን የሚተማመነው የግፍ ገፈት ቀማሽ በሆነው ለነፃነቱና ለመብቱ ለመታገል ከጎኑ ሊያሰልፈው በሚችለው ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ ላይ ብቻ ነው። ከፍተኛ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም ካላቸው አምባገነኖችና ወራሪዎች ጋር የሚደረግ ትግል ሕዝባዊ መሆን አለበት የሚባለው በሰፊ የሕዝብ ድጋፍ ላይ ካልተመሰረተ አሸናፊ መሆን እንደማይቻል ለማሳየት ነው። በሕዝብ ተሳትፎና ድጋፍ ላይ ተመስርቶ ትግል የሚያደርገው ሠራዊትም ሕዝባዊ ሠራዊት፣ ታጋዩም ሕዝባዊ ታጋይ የሚል ስያሜ ያገኘው ለዚህ ነው።

ከወያኔ ጋር ለመፋለም ህይወታቸውን ጭምር በመገበር በአንድ ላይ የተሰባሰቡ ታጋዮች ለከፍተኛ መስዋእትነት የጋበዛቸውን ሕዝባዊና ሃገራዊ ራዕይ ከግቡ ለማድረስ ትግላቸው ሕዝባዊ ትግል እነሱም ሕዝባዊ ታጋዮች መሆናቸውን በሚገባ ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህ በቀላል ቋንቋ የተጻፈ የታጋዮች የኪስ ደብተር የተዘጋጀው ሕዝባዊው ታጋዩ ከወታደራዊ ስልጠና በተጨማሪ ራሱን ሕዝባዊ ሠራዊትና ታጋይ አድርጎ እንዲያይ ለማድረግ ከሚሰጠው ሰፊ የፖለቲካ፣ የራዕይና የመንፈስ ብቃት ግንባታ ትምህርት ውስጥ መሰረታዊ ቁምነገሮቹን በመጭመቅ ነው። የኪስ ሰነዱ ጠቀሜታው ማንኛውም ታጋይ በየትኛውም ወቅት ፋታ ባገኘ ቁጥር ሰለማንነቱና ስለዓላማው ምንነት በማስታወሻነት እንዲጠቀምበትና ሌሎችንም ዓላማውን ማወቅ ለሚፈልጉ ማስተማር የሚችልበትን እድል ለመፍጠር ነው።

ይህ ሰነድ ሕዝባዊ ታጋዩ በልቡና በመንፈሱ ውስጥ በከፍተኛ እምነትና ጽናት ሊይዛቸው የሚገባቸውን የሚከተሉትን መሠረታዊ ቁምነገሮች ያካተተ ነው።

- ሕዝባዊ ታጋዩ የቆመለት ዓላማ ምንድነው?
- ሕዝባዊ ታጋዩ ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ራሳቸውን ሕዝባዊ ታጋዮች ብለው ከሰየሙ ታጋዮች የሚለየው ምንድነው?
- ይህ ሕዝባዊ ታጋይ ከዚህ ቀደም ሌሎች ሊያሳኩት ያልቻሉትን የሕዝብ ምኞትና ፍላጎት ለምን እኔ ማሳካት እችላለሁ ብሎ ያምናል?
- ሕዝባዊ ታጋዮች የሚገነቡትን ሠራዊት እውነተኛ ሕዝባዊ ሠራዊት ለማድረግ ሊመሩባቸው የሚገቡ የሠራዊቱ የውስጥ መርህዎች ምን መሆን አለባቸው?
- ሕዝባዊ ታጋዩ የሕዝብ አመኔታን ድጋፍና ከፍተኛ ተሳትፎ ማግኘት የሚችልባቸው የስነምግባር መመሪያዎች ምንድናቸው?
- ሕዝባዊ ታጋዩ የጠላትን ሃይል እንዴት ይመለከተዋል?

**ዓላማችን ምንድነው?**

- ዋናው ዓላማችን የኢትዮጵያ ሕዝብ በየትኛውም የአስተዳደር እርከን የሚቀመጡ ባለሥልጣኖችን በነፃነት መርጦ የመወከል፣ ካልፈለጋቸውም በነፃነት ከውክልና ማንሳት የሚችልበትን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲመሠረት ማስቻል ነው።
- ሕዝብ እንዲህ ዓይነቱ የመወከል ሥልጣን በእጁ እንዲገባ የሚያስችሉን የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ማንኛውንም መረጃ በነፃነት የማግኘት፣ በነፃነት መሪዎቹን የመምረጥ መብቶቹ ሙሉ በሙሉ እንዲከበሩ ማድረግ ነው።
- የሕዝብ መብቶች ሳይሸራረፉ በተግባር መዋል እንዲችሉና እነዚህን መብቶች ለመቀማትና ለመርገጥ ከሚፈልጉ ማናቸውም አምባገነን ኃይሎች ሕዝብን የሚከላከሉ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ማስቻል ነው።
- መብቶች ተሟልተው በተከበሩበት ሁኔታ በሚያደርገው ነፃ ተሳትፎና ውሳኔ፣ ሕዝብ ራሱንና ሃገሩን የሚጠቅሙ ውሳኔዎች መወሰን፤ በሃገራችን የሚገኙትን ማናቸውን የተወሳሰቡ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ የአስተዳደራዊ፣ የፍትህ፣

የእኩልነት ችግሮች መፍታት የሚችል ብስለትና እውቀት ያለው መሆኑ ከልብ በመቀበል ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት የቆመ ዓላማ ይዘን የተነሳን ነን። ከዚህ ዓላማ የላቀ የሚያስተባብረን፣ በጋራ መስዋእትነት እንድንከፍል የሚያደርገን ሌላ የግል ሆነ የቡድን አላማ የሌለን ታጋዮች ነን።

1. **ለሕዝብ መብትና ነፃነት ቆመናል በማለት በሃገራችን ተነስተው ከነበሩ የፖለቲካና ወታደራዊ ኃይሎች በምን እንለያለን? እኛስ እንደነሱ ወታደራዊ ጉልበታችን ሲፈረጥም የሕዝብ መብት ለመግፈፍ የማንችልበት ምክንያት ምንድነው?**

- ልዩነታችን የምድርና የሰማይ ያህል ነው። ማናቸውም ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝብ ስም መሳሪያ ይዘው ሥልጣን ላይ የመጡ ኃይሎች የእኛን አይነት ዓላማ አንግበው አልተነሱም። ሁሉም ይከተሉት ከነበረው የግራ የፖለቲካ ርእዮተ ዓለም የተነሳ በሃገር ውስጥ ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ በስተቀር ሌሎች መኖር የለባቸውም ባዮች ነበሩ። ሕዝብ የተለያዩ ምርጫዎች ቀርበውለት የፈለገውን መርጦ በነፃነት ሥልጣን ላይ ማውጣት ይችላል የሚል እምነት በድርጅታዊ ፕሮግራማቸው ውስጥ አልነበራቸውም። ስለሕዝብ መብትና ነፃነት ሲያወሩ እነሱ ያለምንም ሌላ አማራጭ በብቸኛ ፓርቲነት በሚገዙት ሃገር ውስጥ በነሱ ፈቃድ ስለሚሰጥ ነፃነትና መብት እንጂ ከነሱ ፈቃድ ውጭ በህገ መንግስት በተደነገገና ይህን ድንጋጌ ማስከበር በሚችሉ ነፃ መንግስታዊ ተቋማት ጥበቃና እንክብካቤ ስለሚደረግለት የሕዝብ መብት አስበው አያውቁም። አባላትና ታጋዮቻቸውንም ያሰለጠኑትና ያስተማሩት የፓርቲውን ብቸኛ የሕዝብ ተወካይነት ተቀብለው የፓርቲው አመራር የሚያዘውን እንዲፈጽሙ እንጂ የሕዝብ ፍላጎት ምን እንደሆነ ማወቅ የሚቻልበትን ነፃና የተለያዩ አማራጮች ያሉትን የፖለቲካ ሥርዓት ለመመስረት አልነበረም። ሁሉም የመሣሪያ ትግል ያደረጉ፣ ሥልጣን በመያዝ የተሳካላቸውም ሆነ ያልተሳካላቸውም ድርጅቶች በሃገሪቱ ውስጥ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ተደራጅተው ለሕዝብ ሃሳባቸውን አቅርበው ሕዝብ የመረጠው ሥልጣን የሚይዝበትን ሁኔታ ለመፍጠር ታግለው አያውቁም። የእነሱ ዓላማ "አርቆ አሳቢ" የሆነው የእነሱ ግንባር ወይም ፓርቲ በብቸኛነት ሥልጣን እንዲይዝ፣ ሥልጣን ይዞም የሕዝብን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች ብቸኛ ፈቺ ሆኖ የሚቀርበት የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ነበር። ስለዚህም ነው ሥልጣን ላይ ሲወጡ ሕዝብ በነፃነት በሚያደርገው ምርጫ መሪዎቹን እንዲመረጥ ያልፈቀዱት። ስለዴሞክራሲ፣ ነፃነትና መብት የሚናገሩት የሚጽፉት ነገር ቢኖራቸውም እነዚህ ቃላት ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ከመዋላቸው ውጭ በተግባር የሚተረጎሙ ጉዳዮች እንዳይሆኑ ያደረጋቸውም እነዚህ ድርጅቶች እኛ ዓላማ አድርገን የተነሳንለትን የዴሞክራሲ ሥርዓት ለማቆም የተነሱ ስላልነበሩ ነው። እንዲያውም ከእነሱ ፓርቲ አመራር ውጭ ለሕዝብ የሚሰጥ የመወሰን ነፃነት የአድሃሪያንና የፀረ ሕዝቦች አመለካከት ነው በማለት ታጋዮቻቸውንና ካድሬዎቻቸውን ሲያስተምሩ ሕዝብን ሲያደኖቁሩ የኖሩበት እምነት ነው። ከነዚህ ኃይሎች የሕዝብን በነፃነት የመወሰን መብት የሚያስከብር የፖለቲካ ሥርዓት መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ ከመጠበቅ ልዩነት የለውም። ድርጅቶቹ የተፈጠሩት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት ስላልሆነ በሕዝብ ስም መማላቸውንና ትግል ማድረጋቸውን ብቻ በማየት ዴሞክራሲ ማምጣት አልቻሉም የሚል ክስ ትክክል አለመሆኑን መረዳት ይኖርብናል። የታገሉት የአንድን ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ለማረጋገጥ ስለሆነ ይህን ማሳካት ችለዋል። ደርግ ለ17፣ ወያኔም ከሃያ አመታት በላይ በሥልጣን በመቆየት የታገሉለትን የአንድ ፓርቲ የበላይነት ዓላማ አሳክተዋል። በእነሱ ዓይን የታገሉት ለዚህ ስለሆነ ለብቻቸው እረጅም ሥልጣን ላይ መቆየታቸው ነውር ሳይሆን ታላቅ ድል አድርገው ቆጥረውታል።

2. **ይህ ሕዝባዊ ታጋይ ከዚህ ቀደም ሌሎች ሊያሳኩት ያልቻሉትን የሕዝብ ምኞትና ፍላጎት ለምን "እኔ ማሳካት እችላለሁ" ብሎ አመነ?**

- የኛ እና ከዚህ ቀደም የሕዝብን በደልና መከራ መሠረት አድርገው በሃገራችን ትግል ያደረጉ ድርጅቶች ልዩነት እኛ ገና ከጅምሩ የቆምነው አንድን ግንባር ወይም ፓርቲ ሥልጣን ላይ ለማውጣት ሳይሆን ሕዝብ የፈለገውን የፖለቲካ ፓርቲ ሥልጣን ላይ ማውጣት የሚችልበት፣ የሕዝብ መብት የተከበረበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመመስረት ነው። የታጋዮች ስልጠና እና ትምህርትም ይህን አመለካከት መሠረት ያደረገ ነው። የድርጅታችንም የፖለቲካ ፕሮግራም የሚያሳየው ይህ ዓላማ ዋናው ዓላማው እንደሆነ ነው። የተመሠረትነውም፣ የምንታገለውና መስዋዕትነት የምንከፍለው እንደቀድሞዎቹ ግንባሮችና ፓርቲዎች የአንድ ፓርቲ ውሎ አድሮም (በመንግሥቱ ኃይለማሪያምና በመለስ ዜናዊ እንደተከሰተው) የአንድን ግለሰብ አምባገነናዊ አገዛዝ በሃገር ላይ ለማስፈን አይደለም። ሕዝብ የናፈቀው በራሱ ፍላጎትና ምርጫ የቆመ መንግሥታዊና ፖለቲካ ሥርዓት ማምጣት እንችላለን የሚለው ልበ ሙሉነታችን የሚመነጨው በሕዝብ ለሚመረጥ መንግሥታዊ ሥርዓት ከውልደታችን ጀምረን አቅደን አምነንበት የምንታገልለት ጉዳይ ስለሆነ ነው። ታጋዮች ለራሳቸውም ለሕዝብ ቃል ኪዳን የሚገቡት፤ መስዋእትነትም የሚከፍሉት በዚህ መሠረታዊ እምነት ላይ ቆመው በመሆኑ ካለምነው ዓላማ ለመድረስ ከማንም የተሻለ ብቃት፣ ዝግጅትና የእምነት ጽናት ይዘን መገኘታችን ነው።

- “የተቋቋምነውና ትግል እያደረግን ያለነው በሃገራችን ቀድመው ከታዩት ድርጅቶች በተለየ በሕዝብ ነፃነት ላይ የቆመ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት ቢሆንም አቅማችንና ጉልበታችን እያደገ ሲመጣ ይህንን እምነታችን ላለማጠፋችን ምን ዋስትና አለው?” የሚል ተገቢ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። የአንድ ፓርቲ የበላይነትን ለማቆም የታገሉ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ በርካታ ፓርቲዎች በአንድ ሃገር ውስጥ በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ፣ የሚል አላማ አንግበው ትግል አድርገው ወይም ሥልጣን ይዘው ይህን አላማቸውን ከደው ፈላጭ ቆራጭ የሆኑ ኃይሎች በታሪክ አጋጣሚዎች ስላሉ ሕዝባዊ ሠራዊቱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እፈጥራለሁ ስላለ ብቻ ይፈጽመዋል ብሎ ማመን አይቻልም። ከምሥረታ ጀምሮ በሕዝባዊ ሠራዊቱ አመራርና በሕዝባዊ ታጋዩ ውስጥ ይህ እምነት ሥር እንዲሰድ ሳያቋርጥ የተሰሩ አመርቂ ሥራዎች፤ በዚህ እምነትና ግንዛቤ ላይ የተገነባ የሕዝብ ተሳትፎና ድጋፍ፤ እንዲህ አይነቱን የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ እንዳይከሰት ማድረግ የሚችሉ በትግል ወቅት የሚደረጉ የተለያዩ ፖሊሲዎች ካላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ትብብርና ሌሎችም በተግባር መፈጸም ያለባቸውን ሥራዎች በመሥራት ብቻ ነው ለሕዝብ የገባነው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ቃል ኪዳን እውን ማድረግ የምንችለው።
- ከዚህ በተጨማሪ የሃገራችን ሕዝብ የፖለቲካ ብስለት፤ የዓለም አቀፍ ሁኔታ ፀረ- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶችን ለመመስረት ለሚፈልጉ ሃይሎች የማይመች የሆነበት ሁኔታ ፀረ ዴሞክራሲያዊ የሆኑ አካሄዶችን በማገድ የራሱ ተጽእኖ የሚያደርግ ነው። የምንኖርበት ዘመን ከየትኛውም ዘመን ይልቅ የዓለማችን ሕዝብ ፍላጎትና ምርጫ አድርጎ ያመጣውን የዴሞክራሲ የፖለቲካ ሥርዓት እምነቶች ተፃሮ መቆም የማይቻልበት ዘመን ነው። ሕዝባዊና ሃገራዊ ፋይዳው ታላቅ የሆነውን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓትን በሃገራችን እውን ለማድረግ የተጀመረን የታሪክ ሂደት መጋፋት ከመቼውም በላይ በሃገርና በሕዝብ ላይ የከፋ ወንጀል መፈጸም ተደረጎ የሚታይበት ዘመን ላይ ደርሰናል። እነዚህ ምክንያቶች ተደምረው በሁሉም ሕዝባዊ ታጋዮች ውስጥ የሚፈጥሩት የሞራል ጫና ከማንኛውም ዘመን በላይ በእኛ ላይ የፀና መሆኑ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንድናመራ የሚገፉን ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚያመላክቱ ናቸው። ቃላችን ላለማጠፍ ሌላው ግፊት ከነዚህ ምክንያቶች የሚመጣ መሆኑ በተስፋ የተሞላን ያደርገናል። ከማንም በላይና በተሻለ የእኛ ትውልድ፣ ያደራጀነው ሕዝባዊ ሠራዊትና ታጋይ ዲሞክራሲን በተግባር ለመተርጎም የእውቀት፣ የብቃት፣ የስነልቦናም የተግባራዊነትም ዝግጁነት አለው። የዘመናችንም የታሪክ ግፊት የሚያግዘው ለዴሞክራሲና ለሕዝብ ልዕልና የቆሙ ኃይሎችን ነው። ዓላማችንን እንደምናሳካ በልበ ሙሉነት የምንናገረው በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ነው።

## 3. ሕዝባዊ ታጋዮች የሚገነቡት ሠራዊት እውነተኛ ሕዝባዊ ሠራዊት እንዲሆን ከግንባታው ጋር ተያይዘው መፈጸም ያለባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

እነዚህን ጉዳዮች በተመለከት የምናስቀምጣቸው ነጥቦች በርካታ ናቸው። ሁሉንም በዚህ ሰነድ ውስጥ ማካተት አይቻልም። እንደወሳኝነታቸው በቅደም ተከተል የሚከተሉትን እናስቀምጣለን።

3.1. አንድ ሕዝባዊ ሠራዊት ምንም ያህል ያማረ የተዋበ ሕዝባዊ ዓላማ ቢኖረውም ይህን ዓላማ ማሳካት የሚችለው በታጋዮቹ አማካይነት ነው። የዓላማ ማስፈጸሚያ መሳሪያው ታጋዩ ነው። ይህ ታጋይ ይህን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ባህሪያት፣ እውቀትና ስነልቦና ያለው መሆኑ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ሕዝባዊ ሠራዊት መመሥረትና ሕዝባዊ ታጋይ መሆን ከማንኛውም ነገር ይበልጥ በጠንካራ ወገናዊነት ላይ የተመሰረተ የታጋዮች የርስ በርስ ግንኙነት ይጠይቃል።

በመሆኑም፣

- እያንዳንዱ ታጋይ ህይወትን ጨምሮ ከፍተኛ መስዋእትነት ለመክፈል በአንድ ላይ እንዲሰባሰብ ያደረጉት ጉዳዮች ከሌሎች ጉዳዮች ሁሉ የላቁ መሆናቸውን ዘወትር በአዕምሮውና በህሊናው የያዘው ጉዳይ መሆን ይኖርበታል።
- በገዛ ሃገሩ ራሱና ወገኖቹ ከጎዳና ተዳዳሪ ውሻ ልዩነት በሌለው መንገድ ተዋርደው፣ ተርበው፣ ተዋክበው እንዲኖሩ ያደረገን ዘረኛ ዘራፊ የወያኔን አገዛዝንና ገዥዎችን አምሮ በመታገል ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች መብትና ጥቅም በእኩልነት የሚያስከብር ሥርዓት ለመፍጠር የተሰባሰብን ታጋዮች በማንኛውም ወቅት የጋራ ውርደትንና ስቃይ የፈጠሩልንን የወገንተኛነትና የአንድነት ስሜት ከሚበረዙ ማናቸውም ስሜቶች ነፃ መሆን ይኖርብናል።
- ይህ ትግል ከፍተኛ የእርስ በርስ መተማመን የሚጠይቅ፤ ታጋዮች በገቡት የጋራ ቃል ኪዳን አንዱ ሌላውን አምኖ እራሱን እሳት ውስጥ ለመጨመር በሚደረግ የመንፈስ ዝግጁነት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ፣ የታጋዮችን የጋራና የቡድን ስሜት የሚያናጉ የግለሰብ ባህሪዎችን በሙሉ ከውስጣችን አጥበን ማውጣት ይኖርብናል።
- ሕዝባዊ ታጋዩ ለመተሳሰብና ለመፈቃቀር አንድነትንና ወገንተኛነትን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ባህሪዎች በዝርዝር አውቆ በታጋዩ ውስጥ ሥር እንዲሰዱና እንዲበለጽጉ ማድረግ ይገባዋል። በተመሳሳይም ጎጂ የሆኑትን ባህሪዎችንም በዝርዝር ተረድቶ በሠራዊቱ ውስጥ ቦታ እንዳይኖራቸው ማድረግ ይጠበቅበታል። አንድ ሕዝባዊ ታጋይ በጓዶቹ መሃል እንደብረት የጠነከረ የመተሳሰብና የወገንተኛነት አንድነት ለመፍጠር እንዲችል አምርሮ ሊታገላቸው የሚገቡትን ጥቂት ጎጂ የግል ባህሮች የሚከተሉት ናቸው።

– ሕዝባዊ ታጋይ ውሸትን፣ ቅጥፈትን አምርሮ ይጠላል። የጓዶች ግንኙነት የተመሠረተው በመተማመን ላይ ስለሆነ ውሸትና ቅጥፈት በጓዶች መሃል የሚኖረውን የመተማመን ስሜት የሚቦረቡር በመሆኑ ሕዝባዊ ታጋይ ከጓዶቹ ጋር ይሁን ከሕዝብ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከሃሰትና ከውሸት ከማጭበርበረ  የጸዳ መሆን ይኖርበታል።

– ሕዝባዊ ታጋይ አድሎን፣ ጠባብ የሆኑ የቡድንና የመጠቃቀም ስሜቶችን አምሮ ይጠላል። አድሎና የመጠቃቀም የቡድን ስሜቶች መፈጠር ሕዝባዊ ሠራዊቱ እንደ አንድ ሃይል በጠላት ላይ መዝመት የሚያስችለውን አቅም ይነሳዋል። ሁሉንም ጓዶቹ በእኩልነት የማይመለከት ታጋይ ለሕዝባዊ ሠራዊቱ መከፋፈልና ምክንያት የሚሆን መርዝ እየዘራ እንደሆነ ማወቅ ይኖርበታል።

– ሕዝባዊ ታጋይ የጓዱን ሰብዓዊ ክብሮች የሚነኩ አመለካከቶች እምነቶች አይኖሩትም፤ ካሉትም ታግሎ ያሸንፋቸዋል። በተመሳሳይም ጓዱን የሚነኩ ድርጊቶችን አይፈጽም። መዋረድ፣ መገፋት መሮት እነዚህን አስወግዳለሁ በማለት በፈቃዱ የመጣን ታጋይ በቋንቋው፣ በባህሉ፣ በሃይማኖቱ በስሙ በቁመናው፣ በመልኩ፣ በፆታው፣ በእድሜው፣ በእውቀት ደረጃው ወይም በሌሎች በማንነቱ ዙሪያ ክብሩና ስሜቱን የሚጎዱ ማናቸውን አመለካከቶች፣ ንግግሮች ድርጊቶች መፈጸም መከፋፈልን ያለመተማመንን መቃቃርን የሚያስከትል ብቻ ሳይሆን ታጋዩ የሚታገልለትን የዜጎች እኩልነት ዓላማ የሚፃረር በመሆኑ አንድ ሕዝባዊ ታጋይ ከእነዚህ ጎጂ ባህሪዎች ነፃ መሆን ይገባዋል።

– ሕዝባዊ ታጋዩ ግለኛነትና ስግብግብነት አምሮ የሚጠላ ነው። ሕዝባዊ ታጋዩ በጓዶቹ መካካል የሚኖረውን መተማመን አንድነት ማጥበቅ የሚችለው በማንኛውም አጋጣሚ ጓዶቹን ሲያስቀድም ነው። ለአንድ ሥራ በጎ ፈቃደኛነት ሲያስፈልግ “እኔ” ብሎ ከጓዶቹ ቀድሞ በመገኘት፣ መስዋዕትነትና አደጋ በሚጠይቁ ፈታኝ ወቅቶች “እኔን ከጓዶቼ አስቀድሙኝ” በማለት የሚንቀሳቀስ ነው።  ምግብና መጠጥ በሚከፋፈሉበት ወቅት እንኳን ሳይቀር ጓዶችን “እናንተ ቅደሙ እኔ እደረሳለሁ” የሚል፣ ሁሉም ጓዶች በአካላዊ ሆነ በሌሎች ጉዳዮች እኩል አቅም ስለማይኖራቸው የጓዶቹን ችግር በመረዳት ሊደግፋቸው ሊያግዛቸው ዝግጁ የሆነ ነው። አቅሙና ብቃቱ እስካለው እንደሱ አቅምና ብቃት ከሌላቸው ጓዶች የላቀ የሥራ ሸክም ለመሸከም ፈቃደኝ የሚሆን፣ ድርጅቱንና ጓዶቹን ሊጎዳ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ እልህ የማይገባ መጥፎ  ፉክክር ውስጥ የማይወድቅ ነው። በጓዶች መሃል ከፍተኛ ፍቅርና መተሳሰብ እንዲኖር ማድረግ እና ጠንካራ የወገንተኛነትና የመፋቀር ስሜት መገንባት የሚቻለው በእንዲህ ዓይነት ባህርይና ሥነምግባር እንደሆነ እያንዳንዱ ሕዝባዊ ታጋይ ሊያውቅ ይገባል።

– ሕዝባዊ ታጋዩ አሉባልታን ሴራን የሚጠላ ነው። አሉባልታና ሴራ እንደብል የታጋዮችን አንድነትና ወገናዊነት ቦርቡረው የሚጨርሱ መሆናቸውን ያውቃል። አንድ ታጋይ በመሪዎቹ ወይም በጓዶቹ ላይ የሚያያቸው ድክመቶች ወይም በእነሱ የተሰሩ ጥፋቶች ካሉ በግልጽ በፊት ለፊት መናገር እንዳለበት የሚያምን ነው። እውነትን አጥብቆ መያዝ ብቻውን በቂ አይደለም። እውነትንና ግልጽነት በአንድ ላይ መያያዝ ካልቻሉ በታጋዩ አንድነትና ወገናዊነት ላይ የሚያመጡት ጉዳት ቀላል አይሆንም። በድብቅ በአሉባልታ  መልኩ የሚሠራጩ እውነተኛ የሆኑ የግለሰቦች ይሁን የድርጅት ስህተቶችና ድክመቶች በአደባባይ በግልጽ ከሚነገሩ የተሳሳቱ ወይም በውሸት ላይ ከተመሠረቱ ጉዳዮች የላቀ ጉዳት እንደሚያስከትሉ ታጋዩ ሊያውቀው ይገባል። በግልጽነት የተነገረን በሃሰት ላይ የተመሰረተን ጉዳይ በቀላሉ ማጥራትና መዝጋት ሲቻል፣ ግልጽነት በጎደለው መንገድ በአሉባልታ መልኩ የሚሠራጭ እውነተኛ ችግር ግን ትልቅ ጉዳት ከማድረሱ በፊት መፍትሄ ማፈላለግ አይቻልም።

– ሕዝባዊ ታጋይ ጓዶች ስህተት ሲሠሩ ከማረም በይሉኝታ ወይም በአድር ባይነት አያልፍም። እሱም ቢሆን ስህተቱንም ለሚነግሩት ጓዶች ክብር እንጂ ጥላቻ አይኖረውም። ሕዝባዊ ታጋይ ድክመቶቹንና ስህተቶቹን እርስበርሱ እየተራረመ መሄድ ካልቻለ ሌላ የሚያርምለት ኃይል እንደሌለ ያውቃል። ድክመቶችና ስህተቶች በግዜ ካልታረሙ መጨረሻው የጋር ውድቀት እንደሆነ  ያውቃል። ከፍተኛ የጓዶችንና የሕዝብን እልቂት የሚያስከትል ሊሆን ይችላል። ስለዚህም በምንም አይነት የራሱንም ሆነ የሌሎችን ስህተቶችና ድክመቶች በግልጽ ለመናገርና እርማት እንዲደረግባቸው ለማድረግ አይሰንፍም። ሕዝባዊ ታጋዩ የጓዶችን ስህተት ለማረም ትልቅ ስብሰባ ወይም የግምገማ ወቅት አይጠብቅም። ወንድማዊ እና እህታዊ በሆነ መንፈጽ ስህተት የሚፈጽሙትን ጓዶቹን እዛው አርሞ ጉዳዩን እዛው የሚጨርስ ነው። የጓዶችን ስህተቶች ወንድማዊና እህታዊ መንገድ ለማረም በወቅቱ ሙከራ ሳያደርግ ጥፋቶችንና ስህተቶችን አጠራቅሞ  ጓዱን ወቅት ጠብቆ ለመወንጀያነት አይጠቀምም። ሕዝባዊ ታጋይ ስህተት በማረምና በሆነ ባልሆነው ጓዶችን በመነዝነዝና በመጨቅጭቅ መሃከል ያለውን ልዩነት ያውቃል።

– ሕዝባዊ ታጋይ የራሱን የጓዶቹን የድርጅቱን ጥንካሬና ድክመቶች፤ የተሠሩ ሥራዎችን ውጤቶች በልበሙሉነት ለመገምገም አያመነታም። ይህ ግምገማ ግን በወያኔ በመሰል ድርጅቶች ውስጥ እንደሚደረገው አባላት እርስ በርሳቸው እንዲሰላለሉ ወይም አመራሩ ወይም ታጋዩ በግሉ የማይወደውን ሰው ለማጥቂያ ተደረጎ ሲሠራበት ካያነው አሠራር የተለየ ነው። ለዴሞክራሲ የቆመው ታጋይ ጓዱን የሚያርመው የሚነቅፈው የተሻለ አቅምና ብቃት እንዲኖረው ለማስተማር እንጂ ቅስሙን ለመስበር ወይም ለማንኳሰስ አይደለም። በጓዶች ለሚሰሩ ስህተቶች ወያኔ  እንደሚያደረገው መሰሪ የሆኑ የግለሰብ ፍላጎቶች እንዳሉ አድርጎ ግምገማን እንደወንጀለኛ አውጫጭን ማስኬድን ሕዝባዊ ታጋዩ አይቀበልም። ጓዶቹ ሆን ብለው ድርጅታቸውንና ከጎናቸው የተሰለፈን ጓዳቸውን ለመጉዳት የተሰለፉ አድርጎ ለሚፈጽሙት ማንኛውም ስህተት ለሚያሳዩት ድክመት የመወንጀያ ምክንያት ማፈላለግ ታጋዮችን አስተማሪ ከሆነ መተራረም የሚያርቅ በመሆኑ ታጋዩ እንዲህ ዓይነቱ ጎጂ የግምገማም ሆነ የእርማት አካሄድን አምርሮ የሚታገል ነው።

- ሕዝባዊ ታጋዩ የቆመለትን ክቡርና ትልቅ አላማ ሊያስረሱ ሊያሰናክሉ ከሚችሉ የግል ስሜት መጎዳቶች የራቀ ነው። በርካታ ታጋዮች በጋራ በሚኖሩበት ሰፊ መዋቀር በተዘረጋበት ድርጅት ውስጥ የግለሰብ ስሜቶችን፣ ክብር ፍላጎትን የሚጎዱ ድርጊቶች በግለሰብና በተቋምም ደረጃ ሊፈጸሙ ይችላሉ። ሕዝባዊ ታጋዩ እነዚህን የግል ስሜት የሚጎዱ ድርጎቶች በሥርዓት እንዲፈቱ ከማድረግ ውጭ ትልቁን ዓላማውን ሊያስረሱ በሚችል ደረጃ እልህ አይጋባም። ለምን ተነካሁ ያዙኝ ልቀቁኝ አይልም። ተጎዳሁ በሚል ስሜት ሌሎች ጓዶቹን የገዛ ድርጅቱን ሊጎዱ የሚችሉ ድርጊቶች አይፈጽምም። ሌላው ቢቀር ይህ እጅግ ከፉ የሆነ የግፍና የውርደት የአገዛዝ ዘመን እስኪያበቃ፣ በታጋዩ መሃከል የሚኖር ግንኙነት ከፍተኛ ትእግስት የተሞላበት እንደሆነ እያንዳንዱ ታጋይ ማወቅ ይኖርበታል። በየጥቃቅኑ ነገር ከሌሎች ጋር የሚላተም፣ የሚያኮርፍ፣ የሚነጫነጭ ታጋይ ረጅሙን የነፃነት ጉዞ በጋራ ከጓዶች ጋር ተጉዞ መዝለቅ እንደማይችል አውቆ እነዚህ የግሉን ባህርያት አምርሮ ይታገላቸዋል።
- ታጋዩ ግብዝነትን አምርሮ የሚጠላ ነው። ለሌላው ጓዱ ሆነ ወይም ለሕዝብ በሚሰብከውና በተግባር በሚያውለው መሃከል ልዩነት እንዳይኖር ተግቶ የሚሠራው ነው። "ሰው ቃሉን ሆኖ መገኘት ካልቻለ ሰው አይደለም" የሚል ጽኑ እምነት የተላበሰ ሊሆን እንደሚገባው የተረዳ ነው። ሰለ እኩልነት አውርቶ መድሎ ሲፈጽም መታየት የለበትም። ስለነፃነት አውርቶ ሌሎች ሲታፈኑ ዝም የሚል ወይም እራሱ አፋኝ መሆን አይችልም። ሁሉንም ቃሎቹን እምነቶቹን በተግባር በምሳሌነት ለማረጋገጥ ዝግጁ የሆነ መሆን አለበት። በተለይ የኃላፊነት ቦታ የሚይዙ ታጋዮች፣ የሚመሩትን ታጋይ በምሳሌነት መምራትን እንደቁልፍ የታጋዮችን የወገንተኛነት የአንድነት ስሜት ማጠናከሪያ፣ በመሪና በተመሪ መካከል ሊኖር የሚገባውን ጥብቅ ትስስር ማጠናከሪያ መሣሪያ አድርገው በተግባር መተርጎም እንደሚገባቸው የተረዱ መሆን አለባቸው። ይህ ምሳሌያዊነት በአኗኗር፣ በአመጋገብ፣ በጥቅማጥቅም ማግኘት፣ የራስን ስህተት በግልጽ በመናገር፣ ለመታረም ዝግጁ በመሆንና መስዋእትነት ለመክፈል በሚታይ ዝግጁነት የሚገለጽ መሆን አለበት።

### 3.2. ስልጠናና ትምህርትን በተመለከተ

ሕዝባዊ ታጋዩ እውቀት በትግሉ ወቅት ከትግሉም በኋላ ያሰበውን ግብ ለማስፈጸም ቁልፍ መሳሪያ እንደሆነ ማወቅ ይኖርበታል። ሕዝባዊ ታጋይ በጦር ሜዳ ውሎ የሚያሳየው ቆራጥነት በብልሃትና በእውቀት ካልተደገፈ እንደ ጀግና ከመሞት አልፎ የተሰዋለትን ዓላማ ማሳካት አይችልም። ታጋዩ በተለይ በሰው ኃይልና በሃብት የተደራጀን ወያኔን የሚያህል እኩይ ኃይል በጀግነነት ላይ እውቀትና ብልሃት ካልጨመርንበት ማሸነፍ እንደማይችል የሚያውቅ ነው። ወያኔን ለመታገል የሕዝባዊ ሠራዊቱ መሪዎችና ታጋዮች ተመሳሳይ ከሆነ የወያኔ ሠራዊትና መሪዎች የላቀ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ብቃት ያላቸው መሆን እንደሚገባቸው የሚያውቁ ናቸው። ለስልጠና ለትምህርት የሚጠፋውን ግዜ በከንቱ እንደሚባክን ግዜ አያዩም። ሁሌም አዲስ ነገር ለመማርና ለማወቅ ዝግጁ ናቸው። ዘመናችን የእውቀት ዘመን መሆኑን የተገነዘቡ ናቸው። ግፈኞችን በአመጽ የመመከት ሥራ በዘመኑ እውቀት የተደገፈ ሊሆን ይገባዋል። ከወታደራዊ ታክቲክና ስትራተጂ አንስቶ እስከምንጠቀምበት ቁሳቁስ ድረስ አቅማችን እስከፈቀደ ድረስ ዘመናዊ የሆነ እንዲሆን ማድረግ ይገባናል። የፖለቲካ እውቀታችንም የዘመኑን የሕዝባችንን ብቃትና ፍላጎት በሚገባ የተረዳና ያወቀ ሊሆን ይገባዋል። የሥራ አፈጻጸም፣ የሥራ ግምገማ፣ ዘመናዊ ከሆነው በዚህ መስክ ከተገኘ እውቀት ጋር የተገናኘና በዚህ እውቀት የዳበረ ሊሆን ይገባዋል። በእውቀት በጥናት ላይ የተመሰረተ ትግል በሕዝብ ወስጥ ካለው የተጠራቀመ ቁጣ ጋር ተደምሮ ለትግሉ የሚከፈለውን መስዋዕትነትና የትግሉን እድሜ የሚያሳጥረው መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

### 3.3. የሕዝባዊ ሠራዊቱን ንብረትና ሃብት አያያዝ በተመለከት

ሕዝባዊ ታጋዩ በእጁ የሚገቡ የሠራዊቱ ንብረቶች በሙሉ በብዙ ችግርና ፈተና የተሰባሰቡ እንደሆኑ የሚያውቅ ነው። በመከራ ከሚኖሩ ደሃ ወገኖቻችን በእርዳታ ወይም ከሌሎች ኃይሎች በልመና የተገኘ እንደሆነ ይረዳል። ገንዘብን ንብረትን እቃዎችን በቁጠባና በጥንቃቄ የመገልገልን የሞራል ኃላፊነት የተረዳ ነው። ንብረትና ገንዘብ ማጉደል ወይም ያለአግባብ መጠቀም እጅግ አስነዋሪ ድርጊት እንደሆነ ይገነዘባል። ህዝባዊ ታጋይ የድርጅትን ብቻ ሳይሆን የጓዶቹንም አደራ የማይበላ ከፍተኛ የሞራል ስብእና ያለው ነው። ዘመናዊ የንብረት የገንዘብ የቁሳቁስ መቆጣጠሪያ ስልት ይኖረዋል።

### 3.4. የሠራዊቱን ሚስጥር መጠበቅ

የሕዝባዊ ታጋይ ጠላትን ማጥቃያ ሌላው መሳሪያ እንቅስቃሴውን ጠላት እንዳያውቅ በማድረግ፣ ጠላት ባልጠበቀውና ባልተዘጋጀበት ወቅትና ቦታ መምታት ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ ጠላት የሕዝባዊ ታጋዩን ቁጥር የያዛቸውን መሳሪያዎች ስንቅና ትጥቅ፣ የሚንቀሳቀስበት ቦታ ማወቅ በተሳነው ቁጥር በጭፍን የሚደናበር ይሆናል። ጠላት መረጃ ከሌለው ለማጥቃትም ሆነ ለመከላከል ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ አይችልም። በመሆኑም ታጋዩ ማናቸውንም የድርጅቱን ምስጢሮች ማወቅ ለማይገባው ለማንኛውም አካል ለራሱ ለታጋይ ጓዱም ቢሆን አይናገርም። ራሱም ሥራውንና ግዳጅን ለመፈጸም ማወቅ ከሚገባው መረጃ በላይ ማወቅ አይፈልግም። ሁሌም አይሳካምና በጠላት እጅ በሚወድቅበት ወቅት በሚፈጸምበት ሰቆቃ የተነሳ የድርጁትን

ሚስጥር ለጠላት አሳልፎ በመስጠት በቃል ኪዳን ጓዶች ላይ ጉዳት እንዲደርስ አያደርግም። ሕዝባዊ ታጋዩ ለዓላማውና ለጓዶቹ ደህንነት ሲል በጠላት እጅ ወድቆ የጠላት መሣሪያ ከመሆን እራሱን ማጥፋት የሚመረጥ ነው።

### 3.5. ሕዝባዊ ታጋዩ ከብረት የጠነከረ ዲሲፕሊን ያለው ነው።

ሕዝባዊ ታጋይ የድርጅቱን የሥነምግባርና የሥነሥርዓት ደንቦች ያለምንም ማወላወል ያከብራል። የጓዶችን የጋራ ውሳኔ ያከብራል፣ ያስፈጽማል። የወታደራዊ መሪዎቹን መመሪያ ያስፈጽማል። በተረጋጋ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በጭንቅ ወቅትም ሥርዓትና ደንብ የተከተለ የተግባር አፈጻጸም ይኖረዋል።

### 3.6. ጥፋትና ቅጣት

ሕዝባዊ ታጋይ በሠራዊቱ ውስጥ ጥፋትና ቅጣትን በተመለከተ በራሱ ነፃ ውሳኔ ያጸደቀው ወይም የተቀበለው የውስጥ ህግና ደንብ ይኖረዋል። ይህን ደንብ ለሁሉም ያለምንም አድሎ ይፈጽማል። በማናቸውም ሁኔታ ታጋዮች ያለምንም ፍትህ ለረጅም ጊዜ ወንጀለኛ ተብለው የሚታሰሩበትን ሁኔታ በምንም አይነት አይፈቅድም። ለሕዝብ ፍትህ የማግኘት መብት የሚታገል ታጋይ የራሱን ጓዶች ፍትህ የማግኘትን መብት የሚጥሱ ሁኔታዎችን በቸልታ ማለፍ አይችልም።

## 4. ሕዝባዊ ታጋይ የሕዝብ አመኔታን ድጋፍና ከፍተኛ ተሳትፎ ማግኘት የሚችልባቸው የሥነምግባር መመሪያዎች ምንድናቸው?

- ለሕዝብ ከፍተኛ ክብር አለው። ሕዝብን አይንቅም፣ ሕዝብን አያንጓጥጥም። ለሕዝብ ስሜት ስሱ ነው። የማኅበረሰቡን ባህል፣ ወግ፣ ቋንቋ አክባሪ ነው። የማኅበረሰቡን አባላት በእድሜያቸው፣ በጾታቸው፣ በአካላዊ ብቃታቸው፣ በእውቀት ደረጃቸው፣ በሃብታቸው፣ በማኅበረሰብ ቦታቸው/በመደባቸው/ በሙያቸው እንዲሁን በሌሎች ጉዳዮች አይንቅም።
- ለሕዝብ የሚያስተምረውን ራሱ በተግባር የሚተረጉም ነው። በቃሉ በተግባሩ መሃል ልዩ ነት አያሳይም። ቃሉን ሆኖ ይገኛል።
- ከሕዝብ ጋር የሚያቀራርቡትንና ሕዝብን ደጋፊና ተሳታፊ ሊያደርጉ የሚችሉ ጉዳዮች አስቀድሞ ያጤናል፤ ይዘጋጃል። ሕዝቡን ሊጠቅም ሊያገለግል የመጣ መሆኑን፤ ያለሕዝብ ፍላጎት የሚፈጽመው ነገር እንደማይኖር ሕዝብን ያሳምናል።
- ከሕዝብ የሚፈልጋቸው ቁሳቁሶች ድጋፎች በሙሉ በሕዝብ ፈቃድ ብቻ የተለገሱ ወይም ህብረተሰቡ ተገቢ ነው ያለው ዋጋ የተከፈለባቸው፤ በፈቃድ በብድር የተወሰዱና የሚመለሱ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
- በሕዝብ ፊት ነውር ሆነው የሚታዩ ታጋዩን ሊያስገምቱ ከሚችሉ የስካር፣ የዝሙት፣ የሆዳምነት፣ የሱሰኝነት ባህርያት የጸዳ ነው።
- ሕዝቡን ባጋጣሚ ካስቀየመ ይቅርታ ለመጠየቅ፤ ጥፋቱ ትልቅ ከሆነ ማኅበረሰቡ የሚወስንበትን ብይንና ቅጣት ለመቀበል የማያቅማማ ነው።
- አቅሙ በፈቀደ ቁጥር ማኅበረሰቡ የሚያስፈልጉትን ማኅበራዊ ግልጋሎቶች በነፃ ለመለገስ እውቀቱን ጉልበቱን የማይቆጥብ ነው።
- በተለይ ለአረጋዊይና ለህጻናት፣ ለታመሙና ለተቸገሩ ደራሽ ሆኖ መታየት ይገባዋል። የሕዝብ አስከፊ አኗኗር ለመቀየር እንጂ ለመጠየፍ የመጣ አለመሆኑን የሚያሳይ ስብእና የተላበሰ ሊሆን ይገባዋል።
- ሕዝባዊ ታጋይ የወያኔ ግፈኛ ሥርዓት ሕዝብን በማስገደድ በማስፈራራት ሕዝባዊ ሠራዊቱን እንዲቃወም፣ ድጋፍ እንዳያደርግ፣ ስለሕዝባዊ ሠራዊቱ መረጃ እንዲያስተላልፍ ሊያደርገው እንደሚችል ያውቃል። ሕዝብ በገዥው መንግሥት ተገዶ ለሚሠራቸው ሥራዎች በሕዝብ ላይ ቂም የሚይዝና የበቀል እርምጃ የሚወስድ አይሆንም። ሕዝብን በማስፈራራትና በማስገደድ ሳይሆን የሕዝብን ልብና መንፈስ በማሸነፍ ወገን ማድረግ ብቸኛው የድል መንገድ መሆኑን ያውቃል።
- በተመሳሳይም ከጠላት ጋር በመወገን ሕዝብን የሚያሰቃዩ ቅጥረኞችን፣ ጥፋታቸውን ግምት ወስጦ ያስገባ ደረጃውን የጠበቀ ቅጣት በመቅጣት የሕዝብ የፍትህ ጥያቄና የሕዝባዊ ሠራዊቱን አለኝታነት ማረጋገጥ ይኖርበታል። በኅብረሰቡ ውስጥ ሕዝባዊ ሠራዊቱ በዘፈቀደ በግለሰቦች ላይ እርምጃ የማይወስድ በቅድሚያ ለማስተማርና ለማስጠንቀቅ የሚሞክር፣ ይህን አልፈው በተገኙ ሰዎች ላይ እርምጃ በሚወስድበት ወቅትም ህብረተሰቡ ሕዝባዊ ሠራዊቱ የሚወስደውን እርምጃ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበት አሠራር መዘረጋት አለበት። እራሱም ስህተት ሲፈጸም ይቅርታ ለመጠየቅ አቅም በፈቀደ ካሳ ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለበት።

- በአጠቃላይ ታጋዩ ለሕዝብ የመጣ እንጂ በሕዝብ ላይ የመጣ እንዳልሆነ፤ የሚከፍለው መስዋዕትነት ለሕዝብ እንደሆነ በማኛውም ድርጊቱ እያረጋገጠ መሄድ ያለበት መሆኑን መዘንጋት የሌለበት ነው።

## 5. ሕዝባዊ ታጋዩ የጠላትን ሃይል እንዴት ይመለከተዋል?

- ለዴሞክራሲና ለሕዝብ መብት መታገል ማለት ከጠላት ጋር በሚደረግ ትግል መወላወል ወይም ቆራጥ እርምጃ አለመውሰድ ማለት አይደለም። ለዴሞክራሲ የተደረጉ ትግሎች ባላንጣዎቻቸውን ማሸነፍ የቻሉት በየትኛውም ግጥሚያ ከጠላቶቻቸው በላይ አምርረውና ቆርጠው በመታገላቸው ነው። አርቆ አሳቢ ማለት የመቁረጥ ውሳኔ የመስጠት አቅምና ብቃት የሌለው ኃይል መሆን ማለት አይደለም። ህዝባዊ ታጋዩ በታሪካችን አርቆ አሳቢ ኃይሎችና ጠባብ ጥቅማቸውን የሚያሳድዱ ኃይሎች ተፋጠው በቆሙባቸው ወቅቶች በሙሉ ጠባብ ጥቅማቸውን ለማስከበር የተነሱ ኃይሎች ለምን ማሸነፍ እንደቻሉ ከታሪክ ትምህርት የቀሰመ ነው።
- ለዴሞክራሲ የሚታገል ኃይል ለጠላት ርህራሄ የሚያሳየው ጠላትን አቸንፎ በሙሉ ቁጥጥሩ ስር ባስገባበት ወቅት ነው። ከዚህ ውጭ ጠላት አነስተኛ ብርታትና ጉልበት በያዘበት ወቅትም እንኳን ቢሆን የመላላት የመናቅ አመለካከትና እርምጃ አይወስድም።
- ለዴሞክራሲ የሚታገለው ኃይል እጅግ ሰፊ የሆነው የጠላት አገልጋይ፣ ወታደር፣ ሰላይን ወዘተ እንደማንኛውም የማኅበረሰቡ አባል፣ በነፃነት በዴሞክራሲ በሰላምና በብልጽግና መኖር የሚፈልግ መሆኑን ያውቃል። ተገዶ ወይም የቀን ጉርሱን ፍለጋ ተቀጥሮ የሚሠራ መሆኑን ይረዳል። ይህ ኃይል ከጠላት እንዲከዳና በጠላት ላይ እንዲያምጽ ሰፊ ቅስቀሳ ያደርጋል፤ ትምህርት ይሰጣል። በተለያዩ አጋጣሚዎች በእጁ የሚወድቁትን የጠላት አገልጋዮች በትህትና፣ በወግና በሥርዓት በመያዝ የሕህዝባዊ ትግሉን ፍትሃዊነት በማስረዳት ከጎኑ እንዲሰለፉ ካልሆነም ደግሞ ከጠላት ጎን ተመልሰው እንዳይሰለፉ ማድረግ ይኖርበታል።
- ሕዝባዊ ታጋይ በማንኛውም ሁኔታ በተማረከ ግለሰብ ወይም እስረኛ ላይ ሰቆቃ አይፈጽምም። ሚስጥር ለማወቅና መረጃ ለማግኘት ከሚኖር ጉጉትና ግፊት ተነስቶ ሰዎችን ለማሰቃየት የሚኖርን ግፊት የሚቋቋም ነው።
- ሕዝባዊ ሠራዊቱ በርካታ የጠላት ወገን በእጁ በሚገባበት ወቅት አቅሙን ግምት ውስጥ በማስገባ ሰዎችን በምግብ በመጠጥ በበሽታ በሌላውም ነገር ሳይሰቃዩ ባስቸኳይ አስተምሮ ወደ መጡበት እንዲመለሱ ወይም ከጎኑ እንዲሰለፉ ማድረግ ይኖርበታል። ያለውሳኔና ያለፍትህ የጠላትን ኃይል ዝም ብሎ በእስር አጉሮ አያሰቃይም።
- በሕዝብ ላይ ግፍና በደል የፈጸሙ የጠላት ኃይሎች በተለይ በአመራር ደረጃ የሚገኙ ኃይሎች ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርበታል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ተከብራ ትኑር!